# የእሳት የአስመራ ጉዞና የኢሳያስ ቃለ ምልልስ

የእሳት የአስመራ ጉዞ ከግንቦት 7 ጋር የተያያዘ መሆኑን ለማወቅ ነብይ መሆን የሚያስፈልግው አይመስለኝም መለስ ብለን የምናስታውስ ከሆነ የግንቦት 7 ድርጅት ሞተር ተደርጎ የሚታሰበው ዋና ፀሀፊው አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ በወያኔ ተይዘው ከታሰሩ ቦኅላ ግንቦት 7 እንደ ድርጅት እንኩዋን ተመጣጣኝ እርምጃ ሊወስድ ቀርቶ ከህዝባዊ ስብሰባ የዘለለ ምንም ነገር ሳይሰራ 6 ወራትን በማስቆጠሩ በአባላቱና ደጋፊዎቹ ዘንድ ግራ መጋባትን ከመፍጠሩም ባሻገር የተለያዩ ፅሁፎች በግንቦት 7 ላይ መውጣት የጀመሩበትና ጠንከር ያለ ትችት የሚሰነዘርበት ጊዜ ነበር የግንቦት 7 አመራሮችም ይህንን የህዝብ ጫናና ግፊት ለማስተንፈስ የሚከተሉትን ሁለት ነገሮች ይዘው ቀረቡ

1 ከአርበኞች ግንባር ጋር ውህደት ልንፈፅም ነው

2 የድርጅታቸውን አይን እና ጆሮ የሆነውን እሳትን ወደ አስመራ መላክ ነበር

1 ከአርበኞች ግንባር ጋር ውህደት ስለመፈጸም

የኢትዮጵያን ፖለቲካ ለሚከታተለው ሁሉ ይሄ ዜና ድንገተኛና እንቆቅልሽ ነበር ምክንያቱም የድርጅቱ አቋም አቶ አንዳርጋቸው እስከታሰሩበት ጊዜ ድረስ ከአርበኞች ግንባር ጋር መስራት እንደማይፈልጉ ግንባሩም ሆነ አመራሩ ደካማና የዴሞክራሲያዊ አሰራር በውስጡ የሌለው በመሆኑ አብረው ለመስራት እንደማይፈልጉ ደጋግመው በተለያየ ቃለ ምልልስም ሆነ ህዝባዊ ስብሰባዎች ሲነግሩን መቆየታቸውን የምናስታውሰው ነው ድንገት ተነስተው ከአርበኞች ግንባር ጋር ልንዋሃድ ነው የሚለው የመጣው አቶ አንዳርጋቸው ከታሰሩ ቦኅላ አርበኞች ግንባር ለውጥ አምጥቶ ይሆን አይመስለኝም ግንቦት ሰባቶች ስለ አርበኞች ግንባር ያላቸው አመለካከት አቶ አንዳርጋቸው ከታሰሩ ቦኅላ አንድ በወጣው አውዲዮ ላይ ስለ ግንባሩ መሪዎች እንደተናገሩት ስለመሆኑ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል ማዳመጥ ለሚፈልግ ካሉት ማስረጃዎች አንዱን ለምሳሌ ያህል እነሆ https://www.youtube.com/watch?v=9ebB5G0vGao ግንቦት 7 በዛን ወቅት አብሮ ለመስራት እንቅስቃሴ ሲያደርግ ያስተዋልነው ከኦሮሞ ነጻ አውጪ ነኝ ከሚለው ድርጅት ጋር ለመስራት በዋናነትም ጀነራል ከማል ገልቹ ይመሩት ከነበረው ኅይል ጋር ነበር ይሄንንም በተለያዩ ህዝባዊ ስብሰባዎች አሳይተውናል ያንን ወቅት መለስ ብለን ካስታወስን የእሳት ዋናው እንግዳም እኚሁ ጀነራል ነበሩ ዛሬ ግን ስለ ጀነራል ከማል ገልቹ የድርጅቱ መሪዎችም ሆኑ የድርጅታቸው ልሳን የሚሉትም ሆነ የሚናገሩት ነገር የላቸውም ለምን ብንል ጀነራሉ በሻዓቢያ የተገፉ በመሆናቸው ግንቦት ሰባትም የሚንቀሳቀሰው የሻዕቢያን ፊት እያየ በመሆኑ ጭምር ነው ሻዓቢያ የጠላውን እየጠሉ የወደደውን እየወደዱ ወዳጅነት የት ድረስ እንደሚወስደን ወደፊት የምናየው ይሆናል ከአርበኞች ግንባር ጋር ውህደት የሚለው ጨዋታ የመጣውም ህዝብና ደጋፊው ለፈጠረው ጫና ማስተንፈሻ እንጂ ሌላ ምንም አይደለም

2 የእሳት ወደ አስመራ ጉዞ

ግንቦት 7 እሳትን ወደ አስመራ የላከው በድርጅቱና በአርበኞች ግንባር መሃል ተፈጠረ የተባለውን ውህደት እንዲዘግብ እግረመንገዳቸውንም በምስል የተደገፈ ድርጅቱ በእንቅስቃሴ ላይ እንዳለ የሚያስመስል ፕሮፖጋንዳ መስራት ነው ለብዙዎቻችን ከምርጫ 97 ቦኅላ ያለውን ጊዜ ካየን በአርበኞች ግንባርም ሆነ በትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄና በሌሎቹም ጭምር ቤዛቸውን አስመራ ካደረጉት ኅይሎች በርካታ ቪዲዮዎችን ተመልክተናል ይህንንም ዩቲዩብ ላይ ሄዶ ማየት ይቻላል ቢሆንም እስካሁን ድረስ ከፕሮፖጋንዳ የዘለለ ነገር ሲደረግ አላየንም ግንቦት ሰባትም ይዞልን የቀረበው ያው የተለመደውን ወታደር በቪዲዮ እያሳዩ አለን እንጂ ሌላ አይደለም ግንቦት 7 እነዚህን ሁለት ነገሮችን በማድረግ በወቅቱ የተነሳውን ጥያቄና እና ግፊት ማስተንፈስ የቻለ ይመስላል አንዳንዶች እንዳውም የእሳት ወደ አስመራ ጉዞ የኢትዮጵያን ትንሳዔ መቃረብ ያሳያል ሲሉም ተደምጠዋል ግንቦት 7 ከተመሰረተ ጀምሮ በየስብሰባ አዳራሹ ከማስጨብጨብ እና ቃለ ምልልሶች በማድረግ ባዶ ተስፋ ከመመገብ ያለፈ ስራ ተሰርቶ አላየንም በተለያየ ጊዜ የተለያየ ነገር በማድረግ የተለያየ አጀንዳ በማምጣት ከህዝብ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ሸውዶ በማለፍ አሁን ያለንበት ደረጃ ላይ ተደርሰዋል ሲደግፉት የነበሩትም ከጊዜ ወደ ጊዜ ከድርጅቱ እየራቁ በተቃራኒው ሻዕቢያዎች አይናቸውን በጨው ታጥበው የግንቦት 7 ደጋፊ ሆነው እያየን እየታዘብን ነው ግንቦት 7 ይህንን ከህዝብና ደጋፊዎቹ ጋር የሚያደርገውን ድብብቆሽ እስከምን ድረስ ይገፋበታል መልሱን የድርጅቱ መሪዎች የሚሰጡት ይሆናል ህዝብና ደጋፊው ግን በቃ የሚልበት ጊዜ መቃረቡ ይታየኛል

## የኢሳያስ ቃለ ምልልስ

የእሳት አስመራ ድረስ ተጉዞ ኢሳያስን ቃለ ምልልስ ማድረግ ለምን አስፈለገ ጥቅሙስ ምንድነው ብለን ብንጠይቅ መልስ መስጠት የሚችል ያለ አይመስለኝም ከግንቦት 7 አመለካከት የምንነሳ ከሆነ ግን መልሱ ቀላል ነው ሁሉም እንደሚያስታውሰው ግንቦት 7 እንደ ድርጅት በተለይም አቶ አንዳርጋቸው እንደ አመራር በተለያዩ መድረኮች ላይ እየቀረቡ አቶ ኢሳያስን ሊያስተዋውቁን ምን ያህል እንደደከሙ የምናስታውሰው ነው አቶ ኢሳያስ ለኢትዮጵያ አንድነት የሚጨነቁ እንደሆኑ ለ30 ዓመታት ያካሄዱት ትግልም ፍትሃዊ እንደነበርም ጭምር እያቀለሸለሸንም ቢሆን ሰምተን ታዝበናቸው አልፈንዋል ዛሬም ቢሆን እሳት ያደረገው ቃለ ምልልስ ከግንቦት 7 አመለካከት እና እምነት ጋር የተያያዘ ነው ግንቦት 7 ሆነ እሳት ኢሳያስ ቅዱስ ነው ብለው ማመን መብታቸው መሆኑ አምናለሁ ችግሩ ይህንን አመለካከታቸውን ህዝብ ላይ ለመጫን መድከማቸው ነው የሚያስተዛዝበው ኢትዮጵያዊው ኢሳያስም ሆነ ሻዕቢያ ምን እና ምን ናቸው ፍላጎታቸውስ ምንድነው የሚለውን ጠንቅቆ ያውቀዋል ከወያኔ ጋር በመሆን ኢትዮጵያ እንድትጠፋ ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም ዛሬም ቢሆን ኢትዮጵያን አፍርሰን እንገነጣጥላለን የሚሉትን ኀይሎች አቅፈው የሚሰሩትን ካየንና በጀት መድበው በሰላዮቻቸው በነ ተስፋዬ ገብረዓብ አማካኝነት ልክ እንደ ወያኔ በኢትዮጵያውያን መካከል ጥላቻና መለያየት እንዲስፋፋ የሚሰሩትን ከተመለከትን ግንቦት ሰባትም ሆነ እሳት ስለ ኢሳያስም ሆነ ሻዕቢያ ሊግቱን የሚፈልጉት ፕሮፖጋንዳ ውሃ አይቋጥርም በድፍረት ይሄንን ጉዳይ ህዝብ ፊት ይዘው መቅረባቸውም እነሱ የሚሉት የሻዕቢያም ሆነ የኢሳያስ ድጋፍ ቅድመ ሁኔታ ያለበት መሆኑን ነው የሚያሳየው ነፃነታችንን ከወያኔ እናስመልሳለን ብለው ለሻዕቢያ ባርነት መዳረጋቸውን ኢሳያስ የሚፈልገውን እስካደረጉ ድረስ ብቻ አስመራ መቀመጥ የሚችሉ መሆናቸውን አስረግጠው እየነገሩን ነው

ቃለ ምልልሱን የታዘብን እንደሆነ የቀረቡትን ጥያቄዎች አንድ በአንድ ስንመረምራቸው አቶ ኢሳያስ የኢትዮጵያ ህዝብ አይን እና ጆሮ ነኝ በሚለው እሳት ሳይሆን በኤርትራ ቴሌቭዥን ቀርበው የራሳቸውን ፕሮፖጋንዳ ለመንፋት የቀረቡ ነበር የሚመስለው በጋዜጠኞቹም የቀረቡት ጥያቄዎች የተመረጡ ለአቶ ኢሳያስ የሚመቹ እንጂ ኢትዮጵያዊው ሊያውቃቸው ይገቡ የነበሩ ጥያቄዎች አልተነሱም ማለት ይቻላል ጥያቄ ማንሳቱ እንኳን ቢቀር አቶ ኢሳያስ ሲዋሹ የኢትዮጵያን ታሪክ የመቶ ዓመት እንደሆነ እየተመፃደቁ ሲነግሩን ሊሞግትዋቸው አልፈለጉም ኢሳቶች ኢትዮጵያዊያንን በተለየም ድርጅታቸው ግንቦት 7 ከሚያካሂደው የትግል አይነት የተለዩትን በተለይም አገር ቤት ያሉትን የተቃዋሚ የፖለቲካ ኀይሎች እንዴት አድርገው እንደሚጠይቁ ለተከታተልን ኢሳያስ ፊት እንደ ህፃን ልጅ ተቀምጠው ቁልጭ ቁልጭ እያሉ አንዳንዴም ፈገግ እያሉ ጌታቸውን ኢሳያስን ልክ ነህ በሚመስል ለማስደሰት ሲያደርጉ የነበረውን ለታዘበ በእፍረት እንደተሸማቀቀ አልጠራጠርም እስቲ በጋዜጠኞቹ የቀረቡትን ጥያቄዎች እንያቸው

1 ጤናው ምን ይመስላል እኛ በምንኖርበት ብዙ ይባላል

2 ለምን ይመስልዎታል ስለ ጤናዎ የሚወራው

3 ያስገረመን ነገር የኤርትራ ባለስልጣናት በነፃነት ነው የሚንቀሳቀሱት ከምን የተነሳ ነው

4 አስተዳደግዎ ማናቸው አቶ ኢሳያስ

5 ልጆች አሉዎት የት ነው የሚማሩት

6 ቀላል ሂወት ነው የሚኖሩት በርሃ ውስጥ ነው ያገኘንዎት

7 ኤርትራ እና ኢትዮጵያ ምን ሁኔታ ላይ ይገኛሉ ረጅሙን ዲስኩር የወሰደው እና የመቶ ዓመት ታሪክ እንዳለን የተማርንበትና እንደ ጲላጦስ ከደሙ ንጹሕ መሆናቸውን የሰማንበት ነው

እነዚህን ጥያቄዎች እና የተሰጡትን መልሶች ላደመጠ የቃለ ምልልሱ ዓላማ ምን እንደነበር ለመረዳት በጣም ቀላልም ነው ከኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው የአቶ ኢሳያስን ስብዕና አሳማምሮ ለመሸጥ የተደረገ ተራ ሙከራ ነው በሌላ በኩልም በኤርትራ ህዝብ ሰቆቃ ላይም መቀለድ  ነው ወደፊትም በሁለቱ ህዝቦች መካከል ሊፈጠር ለሚገባው መቀራረብም ጉዳት እንጂ ጥቅም የለውም እንደ ጋዜጠኛም ሃሳባቸውን በነጻነት ስለ ገለፁ በኤርትራ እስር ቤት በሚማቅቁት የሞያ አጋሮቻችሁ ህይወት ላይም መፍረድ ነው

ከሁሉም እኔን ያናደደኝ የፋሲል የኔዓለም እድሉን አግኝቶ ስለ ኮሎኔል ታደሰ ሙሉነህ ሳይጠይቅ መቅረቱ ነው የኮለኔሉ ልጅ አባቴን አፋልጉኝ ብላ በስብሰባ አዳራሽ ስታለቅስ በቦታው ላይ የነበረ ግለሰብ ነው ያክስተት ልብ የሚነካ እንደነበር በቦታው ላይ የነበሩ በሙሉ የሚያስታውሱት ጉዳይ ነው ሌላው ለጋዜጠኞቹ የነበረኝን አክብሮት በጣም ዝቅ ያደረገብኝ ከኤርትራ ስለተባረሩት ኢትዮጵያዊያን ያቀረቡት ጥያቄ ነው እንደ ጋዜጠኛ ከብዙዎቻችን የተሻለ እውቀት ያላቸው ይመስለኛል በወቅቱም በጋዜጣ ስራ ላይ ከነበሩ የነበረውን ችግር ፅፈው አስነብበውናል በእርግጠኝነትም ስለተባረሩት ወገኖቻችን ያውቃሉ ነገር ግን ጥያቄውን ያቀረቡበት መንገድ የሚያሳዝንና አቶ ኢሳያስም ለውሸት እንዲያመቻቸው ተደርጎ ነበር የቀረበው ጥያቄውም ስለ ተባረሩት ወገኖች ተፅፎ አንብበናል በዚህ ጉዳይ ምን ይላሉ የሚል ነበር በአይናቸው አይተውት የነበረውን እውነታ ዛሬ አቶ ኢሳያስ ለመመለስ እንዲመቻቸው ይህን ያህል መጨነቅ የሚያስተዛዝብ ነው የተፃፈ ሁሉ እውነት ስለማይሆን እባክዎን ያስተባብሉ ብሎ እንደማለት ነው አሁን አሁን ሳስበው በአንዳንድ ጋዜጠኞች ላይ ጥያቄ እንዳነሳ ተገድጃለሁ ሃሳብን በነፃነት ለመፃፍ በተደረገው ሂደት ላይ መስዋዕትነት የከፈሉ ጋዜጠኞች እንዴት ተሰደው በኢዲቶሪያል ፖሊሲ ሽፋን የማያምኑበትን ሊሰሩ ይችላሉ ይህን የምለው ተደጋግሞ ሻዕቢያንም ሆነ ተላላኪውን ተስፋዬ ገብረዓብን አስመልክቶ ሲጠየቁ በኢዲቶሪያል ፖሊሲው መሰረት ስለምንሰራ ነው ብለው ይመልሱ ስለነበር ነው አንድ ሰው የማያምንበትን የሚሰራው ወይ ተገዶ ወይም ከጥቅም ጋር የተያያዘ ከሆነ ብቻ ነው በነፃው ዓለም ደሞ ጥቅም እንጂ ግዴታ የለም በጥቅም ከሆነ ደሞ የሚታመነው አገር ቤት የጋዜጣ ባለቤትም ይሁን ፀሃፊ ተሁኖ  ሲሰራ የነበረው ታምኖበት ሳይሆን ወያኔን የሚያጋልጠው ስራ ወይም ፅሁፍ በህዝብ ይወደድ ስለነበርና ገበያውም የተሻለው እሱ ስለነበር ይሆን መልሱን ለህሊናቸው እተወዋለሁ እውነት መፃፍ ብዙ መስዋዕትነትን በሚጠይቅ ቦታ ላይ እውነትን ሲፅፍ የነበረ ብዕር በነፃው አለም ላይ መዶልዶሙን ስናይ ከጥቅም ጋር የተያያዘ ለመሆኑ ምስክር መጥራት አያስፈልግም ይሄ ግን ሁሉንም አይመለከትም አሁንም ድረስ እውነትን እየፃፉ እኛም እየኮራንባቸው ያሉ በርካቶች አሉ በኢድቶሪያል ፖሊሲ ሽፋን አንድ ጋዜጠኛ የማያምንበትን የሚሰራ ከሆነ እንደ ጋዜጠኛ ነፃነቱን አሳልፎ ሸጥዋል ማለት ነው እምነታችን ይህ ከሆነ በኢትዮጵያ ቴሌቭዥንም ሆነ ራዲዮ ላይ በሚሰሩት ኢትዮጵያዊያን መናደድም ሆነ ማውገዝ አይገባንም ምክንያቱም የሚሰሩት ኢዲቶሪያል ፖሊሲው በሚፈቅደው መሰረት ነው ሰርቶ ለመኖርም ሌላ አማራጭ ላይኖራቸው ይችላል የኛ የምንላቸው ጋዜጠኞችስ ስለ ወያኔና ሻዕቢያ ስንት ነገር እንዳልፃፉ ዛሬ በኢዲቶሪያል ፖሊሲ ሽፋን ከእምነታችን ውጪ እየሰራን ነው ሊሉን ይፈልጋሉ በነፃው አለም እየተኖረ ለመኖርም ብዙ አማራጭ እያለ ስለ ኢዲቶሪያል ፖሊሲ ማውራት እራስን ማስገመት ነው ኢሳትም እንደ አማራጭ ሚዲያ መቀጠል ከሆነ አላማው ከድርጅት ነፃ ሆኖ የሚንቀሳቀስበት መንገድ መፈለግ ያለበት ይመስለኛል የፖለቲካ ድርጅት ሲመሰረት እና ሲፈርስ ብዙ አይተናል የኢሳትም ዓላማ ግንቦት 7 እስካለ ለመኖር ሲጠፋም አብሮ ለመጥፋት ከሆነ እየተከተላችሁት ያለው መንገድ ትክክል ነው ኢሳት ነፃ ሚዲያ ነው የሚል ካለ እሱ እራሱን የሚያታልል ነው በርካታ ማስረጃዎችንም መዘርዘር ይቻላል

በአስመራ በኩል ስለሚካሄደው ትግልና ይገኛል ስለሚባለው እርዳታ እርዳታው ምን ቅድመ ሁኔታ እንደ አለበት ስለሚነገረውና እየሰማን ስላለንው አዲስ አይነት የትጥቅ ትግል ትግሉ በአስመራ በኩል አለ እየተካሄደ ነው ሲባል ያስቆጠረውን በጣም ረጅም ዘመን እና ያስመዘገበውን ባዶ ውጤት ትግል በአስመራ በኩል ይቻላል ብለው በሻዕቢያ ስለተበሉት ኢትዮጵያዊያን ወዘተ ብዙ ማለት ይቻላል ብዙም ስለተባለበት አልሄድበትም

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር

ዜግነት ከምድረ ኦስትሪያ